በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት
ኤጀንሲ

THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN INVESTMENT
**AGENCY**

ቀን 24 ሚያዚያ 2003
DATE

ቁጥር ኢኢቦ/ኤጠ/3/049
REF. No.

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>ለአስጎብኝነት ሥራ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለሚገቡ «አውቶቡሶች» የወጣውን መመሪያ ስለመላክ</u>

በአስጎብኚነት የሥራ መስክ የሚሰማሩ ባለሀብቶች በደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 (ለ) መሠረት «አውቶቡሶችን» ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማስገባት እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም ቦርዱ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት ሚያዝያ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ባደረገው ዘጠናኛ መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀውን «ለአስጎብኝነት ሥራ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለሚገቡ አውቶቡሶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 (ለ) የተደነገገውን ለማስፈፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2003»ን አያይዘን እየላክን መመሪያው ከሚያዝያ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል አስታውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

መኮንን ማንያዘዋል
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ
ሰብሳቢ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Investment Agency

<u>ግልባጭ፡</u>

- ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ

  <u>አዲስ አበባ</u>

## ለአስጎብኝነት ሥራ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለሚገቡ አውቶቡሶች የወጣ መመሪያ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/1994 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ ‹‹ ለአስጎብኝነት ሥራ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለሚገቡ አውቶቡሶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) የተደነገገውን ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2003›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በደንቡ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) መሠረት ‹‹አውቶቡስ›› ማለት ታጣፊ ወንበሮችን ሳይጨምር ቢያንስ 45 መቀመጫዎች ያሉት የሰው ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ነው፡፡

3. **ስለተፈቀደው አውቶቡስ ብዛት**

በአስጎብኚነት ሥራ የተሠማራ/የሚሠማራ ባለሀብት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ የሚፈቀድለት የአውቶቡስ ብዛት 1 (አንድ) ብቻ ይሆናል፡፡

4. **ክትትል ስለማድረግ**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 መሠረት ለአስጎብኚነት ሥራ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ የሚገባን አውቶቡስ ለመለየት በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በሚወሰነው መሠረት የመለያ ምልክት እንዲኖረው ይደረጋል፤ አውቶቡሱ ለተፈቀደለት ዓላማ መዋሉንም እንዲቆጣጠርና እንዲያረጋግጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

5. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 14 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ

መኮንን ማንያዘዋል
የኢ.ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Investment Agency